የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፮
አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.56
ADDIS ABABA 10th July, 2017

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፳፰/፪ሺ፱ ዓ.ም

ለብሔራዊ የጥራት ማረጋገጫ መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ………ገጽ ፱ሺ፮፻፺

## Content

Proclamation No. 1028/2017

International Development Association Financing Agreement for financing the National Quality Infrastructure Development Project Ratification Proclamation…………………………Page 9690

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፳፰/፪ሺ፱

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለብሔራዊ የጥራት ማረጋገጫ መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፴፯ ሚሊዮን ፪፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሠላሣ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል መጋቢት ፳፱ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO.1028/2017

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 37,200,000 Special Drawing Rights (Thirty Seven Million Two Hundred Thousand SDR) for financing the National Quality Infrastructure Development Project was signed in Addis Ababa on the 7th day of April, 2017;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Financing Agreement at its session held on the 22nd day of June, 2017;

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለብሔራዊ የጥራት ማረጋገጫ መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፳፰/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል መጋቢት ፳፱ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5983-ET ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፴፯ሚሊዮን ፪፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሠላሣ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

***አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም***

**ሙላቱ ተሾመ ዶ/ር**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for financing the National Quality Infrastructure Development Project Ratification Proclamation No. 1028/2017".

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Number 5983-ET signed in Addis Ababa on the 7th day of April, 2017, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of SDR 37,200,000 (Thirty Seven Million Two Hundred Thousand SDR) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication on the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, this 10th day of July, 2017**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA**